ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ሚያዝያ 1998 ዓ.ም.

# የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 4

## የኢትዮጵያ ሰፈራ መርሐ ግብር ቅኝት

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡
- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡
- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡
- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን እያካሄደ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለመወያያ የቀረበው ርዕስ *የምግብ ዋስትናን በኢትዮጵያ ማረጋገጥ ይቻላል?* የሚል ነው፡፡
- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

### መግቢያ

በደርግ ዘመን ከ1977 እስከ 1979 ዓ.ም ብቻ ወደ 600,000 የሚደርሱ ሰዎች በሰፈራ መርሐ ግብር ታቅፈው እንደነበር ይታወሳል፡፡ በወቅቱ ሰፈራዎቹ በጥድፊያና ያለበቂ ጥናት በመካሄዳቸው ሳቢያ የእርሻ መሬት ጥበት፤ የመሠረተ ልማት አለመሟላት፤ የነባር ግልጋሎቶች መዳሸቅ፤ እንዲሁም የበሽታዎች መስፋፋት እና የሚቾች ቁጥር መበራከት ተስተውሏል፡፡ ሰፋሪዎቹ የሚመለመሉት በግዴታ ስለነበረ የቤተሰብ መለያየትም ተከስቷል፡፡ ከደርግ አገዛዝ መውደቅ በኋላ አብዛኛዎቹ ሰፋሪዎች ጣቢያዎቻቸውን ለቀው ወደ ትውልድ ስፍራቸው በመመለሳቸው መርሐ ግብሩ ውጤት አልባና አክሳሪ ሆኗል፡፡

የኢፌዲሪ መንግሥት ቀደም ሲል የሰፈራው መርሐ ግብርን ተቃውሞት ነበረ፡፡ ዘግይቶ ግን ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለድህነት ቅነሳ አስፈላጊ ስትራቴጂ መሆኑን አምኖበታል፡፡ በ 1995 ዓ.ም መንግሥት ከለጋሾች እና አጋር የዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመሆን በጋራ አዲስ የምግብ ዋስትና ጥምረትን የመሰረተ ሲሆን ከዚሁ ጋር በማያያዝም በሦስት ዓመታት ብቻ ወደ 2.2 ሚሊዮን ሕዝብ ለማስፈር የድርጊት መርሐ ግብር ነድፏል፡፡ በዚህም መሰረት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ በአራት የመስተዳደር ክልሎች እንዲሰፍር አድርጓል፡፡

ይህን መሰረት በማድረግ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) የሰፈራውን መርሐ ግብር አስመልክቶ ለምን አንዳንድ ሰፋሪዎች ይበልጥ እንደተሳካላቸው እና ራሳቸውን እንደቻሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ለምን ራሳቸውን እንዳልቻሉ ወይም የሰፈራ ጣቢያዎቻቸውን ጥለው እንደሚመለሱ የሚተንተን ጥናት አካሂዷል፡፡ ጥናቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረምረቃ ተማሪዎችና መምህራን በተውጣጡ የተመራማሪዎች ቡድን የተካሄደ ሲሆን ውጤቱም ታህሳስ 1998 ዓ.ም በተካሄደው አውደ ጥናት ይፋ ሆኗል፡፡

ጥናቱ በአማራ ክልል (በሰሜን ጎንደር ዞን)፤ በኦሮሚያ ክልል (በኢሉባቦር፤ በምዕራብ ወለጋ፤ በባሌ እና በምዕራብ ሸዋ ዞኖች)፤ በደቡብ ክልል (በደቡብ ኦሞ እና በወላይታ ዞኖች)፤ እና በትግራይ ክልል (በምዕራብ ትግራይ ዞን) የሚገኙ 11 የናሙና ሰፈራ ጣቢያዎችን በጥልቀት ተመልክቷል፡፡

### የጥናቱ ግኝቶች

1. <u>ሰፈራው በፈቃደኝነት ላይ ስለመመስረቱ</u>

በመርህ ደረጃ ሰፈራው በፈቃደኝነት ላይ እንዲመሠረት የታለመ ቢሆንም መርሐ ግብሩ በተዘዋዋሪ መንገድ በጫና እና በማባበያ ላይ የተመረኮዘ እንደነበረ ጥናቶቹ ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህም መሰረቱ ለሕዝቡ መግለጫ ሲሰጥ የሰፈራው ቦታ አመቺነትና የድጋፍ አቅርቦቱ መጠን በተጋነነ መልኩ በመነገሩ እንዲሁም የድርቅ ተጠቂ በሆኑት አንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች የምግብ እርዳታ ሊቋረጥ እንደሚችል ማስጠንቀቂያ በመሰጠቱ ነው፡፡

2. <u>በጥቅም ላይ ስላልዋለ የእርሻ መሬት</u>

በሰፈራው መርሐ ግብር ዕቅድ አወጣጥ የፌደራል መንግሥት፤ የክልልና የወረዳ አስተዳደሮች ተሳትፈዋል፡፡ ቢሆንም ብዙዎቹ የሰፈራ ቦታዎች የተመረጡት በጥድፊያ ነበር፡፡ ጥናቶቹ እንዳመለከቱት “አለ” ተብሎ የተጠቀሰው ጥቅም ላይ ያልዋለ ሠፊ የእርሻ መሬት በእርግጥም ስለመኖሩ አጠያያቂ ሆኗል፡፡ ለዚህም የቀረበው መረጃ ለሰፈራ የተመረጡት መሬቶች ቀደም ብሎ በአብዛኛው በነባር ነዋሪዎች የተያዘ ወይንም በእጻሪነት የሚጠቀሙበት አልያም ለግጦሽ ወይንም ለደን ልማት ከልለውት የነበረ ስፍራ ሲሆን ለቡና እና ለማር ምርትም የሚያገለግል መሬት በመሆኑ ነው፡፡

*በአንዳንድ ቦታዎች ነባሮቹ ነዋሪዎች ለሰፈራው የታሰበው ቦታ መሬት ለሌላቸው ወጣት ልጆቻችን በቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል ሲሉ በሌላ*

*አካባቢ ደግሞ መሬቱ በቅድሚያ ለእኛ መደልደል አለበት ሲሉ ጠይቀዋል።*

### 3. ከነባሩ ሕዝብ ጋር ስለመመካከር

የሰፈራ ቦታዎችነን በተመለከተ የነባሩን ሕዝብ ይሁንታ ለማግኘት የተለያዩ መድረኮች ቢዘጋጁም የውይይቱና ምክክሩ ትኩረት ባመዛኙ ነባሩ ማኅበረሰብ የሰፈራውን መርሐ ግብር እንዲቀበለው በማሳመንና ለሰፋሪዎቹ መጠለያ እንዲሰራ ማግባባት ላይ ያነጣጠረ ነበር። አብዛኞቹ ስብሰባዎች ይደረጉ የነበረው ከቀበሌ አመራሮች፤ ከአገር ሽማግሌዎች ወይም ከተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ጋር ብቻ ነበር። በአንዳንድ የቀድሞ መንግሥት እርሻዎች ላይ ሰፍረው የነበሩት ሰፋሪዎች "ሕጋዊ አይደላችሁም" ተብለው ከሰፈሩበት ተነቅለዋል። "ነባር ነዋሪዎችም ቋሚ አራሾች አይደላችሁም" ተብለው የተፈናቀሉም አሉ። ለነዚህ ተፈናቃዮች መንግስት ማካካሻ አልሰጠም። ከሞላ ጐደል በሁሉም ሰፈራ ጣቢያዎች አካባቢ በውሃ፤ በደን፤ በከብት ግጦሽ መሬት ላይ ውጥረት ተፈጥሯል። ከአስራ አንዱ የናሙና ሰፈራ ጣቢያዎች በስምንቱ ውስጥ ግጭት ተፈጥሯል። አልፎ አልፎም ሞት ተከስቷል።

*በደቡብ ክልል ምክክር ሳይደረግ ወይም መግባባት ላይ ሳይደረስ ወይም ከነባሩ ሕዝብ የተወሰነው ብቻ በተጽዕኖ እንዲስማሙ የተደረገበት ሁኔታ ታይቷል። በአማራ ክልል በነባሩ ማኅበረሰብ ተቃውሞ ቢነሳም ተቃውሞው ከምንም ሳይቆጠር ሰፈራው ቀጥሏል።*

### 4. የሰፈራ ጣቢያዎች ዝግጅቶች

ኅብረተሰቡ ስለሰፈራው መርሐ ግብር ግንዛቤ እንዲያዳብር በተደረጉ ስብሰባዎች የሰፈራ ጣቢያዎቹ ምቹነት በተጋነነ መልኩ እንደቀረበ ጥናቶቹ ያመለክታሉ። ለእያንዳንዱ ሰፋሪ ቤተሰብ ሁለት ሄክታር ለም መሬት፤ ሁለት የእርሻ በሬዎች፤ ማለፊያ የመኖሪያ ቤት፤ በቂ የጤናና የትምህርት አገልግሎት፤ እስከ ሦስት ዓመት የሚዘልቅ የእርዳታ እህል፤ ወዘተ እንደሚቀርቡ ተስፋ ተሰጥቷል።

ሆኖም ግን ቃል በተገባውና በተግባር በታየው መሃል ሰፊ ልዩነት በመታየቱ ምክንያት በተለያዩ ጣቢያዎች ድርሻቸው ከ 5 እስከ 87 በመቶ የሚደርሱ ሰፋሪዎች ጣቢያቸውን ጥለው ሄደዋል። በሰፈራ ጣቢያ የቀሩት በአብዛኛው እዚያው ለመቆየት የቆረጡ ይመስላሉ። ጠንክ ረውም ሲሠሩ ይታያሉ። መጋቢ መንገዶች ቀደም ብለው ወደ ሁሉም ሰፈራ ጣቢያዎች እንዲያደርሱ ታስበው የተሰሩ ቢሆንም ከፊሎቹ ግን ለበጋ ወራት ብቻ የሚያገለግሉ ሆነው ተገኝተዋል። በብዙ የሰፈራ ጣቢያዎች ሰፋሪዎቹ ቤት ሳይሰራላቸው በመቅረቱና ተሰርተው የነበሩትም ቤቶች ደረጃቸውን ስላልጠበቁ እዚያ ከደረሱ በኋላ ራሳቸው ቤት መሥራት ነበረባቸው።

ወደ መጀመሪያው አካባቢ ለሰፋሪው እህልና አልፎ አልፎም የምግብ ዘይት፤ ባቄላ፤ ስኳርድንች፤ በርበሬ፤ ጨውና ሳሙና በእርዳታ ይታደል ነበር። በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ዕደላው ከስምንት ወራት በኋላ ሲቋረጥ በሌሎቹ ደግሞ ሳይቋረጥ ለሁለት ዓመታት የዘለቀበት ሁኔታ አለ። ባመዛኙ ውሃ የሚቀዳው ከወንዝ፤ ከምንጭና ከጉድጓድ ነው። ሰውም ሆነ እንስሳው ለመጠጥና ለጽዳት የሚጠቀመው ከአንድ ሥፍራ በመሆኑ ለጤና አስጊ ሁኔታ ተፈጥሯል። በአብዛኛዎቹ የሰፈራ ጣቢያዎች አቅራቢያ ትምህርት ቤቶች ቢገኙም በጥቂት ቦታዎች ግን በጣም ርቀው ይገኛሉ።

*የመሬት እጥረት ስላለ ብዙዎች ቤተሰቦች የተሰጣቸው ቢበዛ አንድ ሄክታር መሬት ነበር። የመሬቱ እደላም የቤተሰብ አባላትን ቁጥርና የመሬቱን ለምነት ያላገናዘበ በመሆኑ ከሰፋሪዎች ቅሬታ አስከትሏል።*

## የሰፈራው መርሐ ግብር መርሆዎች ሲገመገሙ

### 1. ሰፋሪው በየራሱ ክልል ስለመስፈሩ

ጥናቶቹ እንደመሰከሩት ሰፈራዎቹ የተካሄዱት በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ ነው። በዚህም ምክንያት የጎሣ ልዩነቶች ወደ ግጭት እንዳያመሩ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህም ሆኖ በአራቱም ክልሎች ጥቂት የጎሣ፤ የባህል ወይም የኃይማኖት ልዩነቶች ነበሩ። ስለሆነም ውጥረትንና ግጭቶችን እንደታሰበው ጨርሶ ለማስወገድ አልተቻለም። የውጥረቱና ግጭቶቹ መነሻ በአብዛኛው የእርሻና የግጦሽ መሬት እጥረት፤ የደኖች እና የውሃ መቅጃ ቦታዎች መጣበብ ናቸው።

*በጣም የተለያዩ ጎሳዎች የሰፈሩበት ክልል ደቡብ ነው። የወላይታና የኮንሶ ደገኞች በሲዳማና በቦዲ አርብቶ አደሮች መሃል እዲሰፍሩ ተደርጓል። ከኃይማኖት አንፃርም የሐረርጌ ሙስሊም ኦሮሞዎች በወለጋ ክርስትያን ኦሮሞዎች መሃል እንዲሠፍሩ ተደርጓል።*

### 2. የአካባቢ ጥበቃና ክብካቤ

የአካባቢ ጥበቃ አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ቢሆንም ለአዳዲስ የእርሻ መሬቶች፤ ለግንባታ፤ እና ለማገዶ ሲባል የሰፈራ መርሐ ግብሩ በከፍተኛ ደረጃ ደን እንዲወድም ምክንያት ሆኗል። ውጤቶቹም የአፈር መሸርሸር፤ የብዝሃ ህይወት መመናመን እና የአየር ፀባይ ለውጥ ናቸው። አንዳንድ የሰፈራ ጣቢያዎች የተመረጡት በደን ክልል ውስጥ ወይም በአቅራቢያው በመሆኑ አንዳንድ አገር በቀል ዛፎችና የዱር አራዊት ዝርያዎች ለመጥፋት ተቃርበዋል። ቀድሞ የነበሩ ባህላዊ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ሥርዓቶችም እንዲከስሙ ተገደዋል።

*ሰፋሪዎች ለንግድም ይሁን ለማብሰያነት ሲባል ከሰል ለማክሰል ትልልቅ ዛፎችን የመቁረጥ ዝንባሌ ያሳያሉ ሲሉ ነባሮቹ ነዋሪዎች ስጋታቸውን ገልጸዋል።*

### 3. የልማት ሂደት

በመጀመሪያው ዓመት በርካቶቹ ሰፋሪዎች በምግብ ሰብል ራሳቸውን ለመቻል አዳግቷቸዋል። በተለይም በእማወራዎች የሚተዳደሩ ቤተሰቦች፤ አዛውንቶች፤ አቅመ ደካሞች፤ አካለ ጎደሎዎች፤ እንዲሁም በተደጋጋሚ በቆላ በሽታዎች የሚጠቁት የሰፋሪ ቤተሰቦች በግምባር ቀደም ለምግብ እጥረት ተጋላጭ ሆነዋል። በብዙዎቹ የሰፈራ ጣቢያዎች የምግብ ዕደላው ከስምንት ወራት በኋላ መቋረጡ ሳቢያ በራስ መተማመን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ይህም ሆኖ አንዳንድ ቤተሰቦች ከሌሎች ቤተሰቦች በጣም የተሻለ ስኬት አስመዝግበዋል። ይህ የሆነው በአብዛኛው ከነበሩበት አካባቢ ቅርስ ይዘው በመምጣታቸው ነበር።

*ይበልጥ ስኬታማ የሆኑት ሰፊ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ያሏቸውና መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ከማኅበረሰቡ፣ ከአስተዳዳሪዎች፣ ከአካባቢው ነዋሪዎችና ከባለሀብቶች ጋር ትስስር ያላቸው በአብዛኛው በአባወራዎች የሚመሩ ቤተሰቦች ናቸው።*

## የወደፊት አቅጣጫ መርህ

ከላይ እንደተገለፀው በመንግሥት፣ በለጋሾች፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግል ባለሃብቶች፣ በነባሩ ሕዝብና በሰፋሪዎች መሃል እንዲኖር ይጠበቅ የነበረው ትብብርና አጋርነት ውሱን ሆኖ ተገኝቷል። አብዛኛውን የሰፈራውን ወጪ የሸፈነው መንግሥት ሲሆን ሌሎቹ የተጫወቱት ሚና እስከዚህም አይደለም። በመንግሥትና በአጋሮቹ መሃል የእርስበርስ አለመተማመን የነበረ ይመስላል። የመንግሥት አጋሮች ለሰፈራው መርሐ ግብር የገንዘብ ርዳታ በበቂ አልለገሱም፣ መንግሥትም ያለችግር ወደ ሰፈራ ጣቢያ እንዲደርሱ ሁኔታዎችን አላመቻቸም።

ሰፋሪዎቹ ራሳቸውን እንዲችሉ መመሪያዎቹ ያስገነዝባሉ። በዚህም መሰረት ሰፋሪዎቹ ቤታቸውን ራሳቸው ገንብተዋል ወይም በድጋሚ አሻሽለው ሰርተዋል፣ እንዲሁም መሬታቸውን ለእርሻ አዘጋጅተዋል። ይህም ክንውን ራስን የመርዳትና ወጪ የመጋራትን ጅማሮ ያሳያል።

የሰፋሪ ተወካዮች የሠፈራ ጣቢያዎችን አስቀድመው እንዲጎበኙ ተልከው ነበር። ሆኖም የጉብኝቱ ስፍራ የእነርሱ ማኅበረሰብ የሚሰፍርበት ጣቢያ ሳይሆን በአብነት ወደተያዙት ጣቢያዎች ነበረ። ይህም ቅሬታ ማስነሳቱ አልቀረም። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ተወካዮቹ ከጉብኝታቸው ሳይመለሱ ሰፋሪዎቹ ተሸኝተዋል።

*የተቀባዩ ማኅበረሰብ ስምምነትና ተሳትፎ የይስሙላ ወይም በጣም ዝቅተኛ የመሆን አዝማሚያ ነበረው። ምንም አይነት ስምምነትና ተሳትፎ ያልነበረበትም ሁኔታ ተስተውሏል። እውነተኛ ተሳትፎ እንዳይኖር እንቅፋት የሆነው የሀብት ምንጭ አጠቃቀም ስጋትና ሊከሰት የሚችለው ሽሚያ ነበር።*

በሰፈራው ሂደት ካለፈው ተሞክሮ መማርና ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል። ከመጀመሪያው ዓመት የሰፈራ እንቅስቃሴ በኂላ መንግሥት ግምገማዎችን ቢያካሄድም በሰፈራው ዕቅድና አተገባበር ላይ ይህ ነው ሊባል የሚችል ለውጥ አልተደረገም።

የጥገኝነት መሰበርና በራስ መተማመን ታልሞ ነበር። አብዛኛዎቹ ሰፋሪዎች ራሳቸውን በመቻል ጐዳና ላይ ይገኛሉ። በቆላማው አካባቢ በሚከሰተው ድርቅ ካልተመቱ በቀር የምግብ እርዳታም ላያሻቸው ይችላል። ይህም ሆኖ ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች አሉ።

እርሻን ብቻ ሳይሆን ትናንሽ የንግድ እንቅስቃሴዎችንም ማስፋፋት እንደሚያስፈልግ የሰፈራ መመሪያዎቹ ይጠቁማሉ። አንዳንድ ስኬታማ ሰፋሪዎችም በንግድ፣ ከብት በመግዛት፣ የእህል ወፍጮ በመትከል፣ ተጨማሪ መሬት በመግዛት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በልፅገዋል። ሰፋሪው ማኅበረሰብ ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆኖ ዕቅዶችን በመንደፍ፣ በመተግበርና ክትትል በማድረግ ሂደት ላይ ንቁ ተሳተፎ ማድረግ እንዳለበት ይታመናል። ይሁን እንጂ ሰፈራው በዘመቻ መልክ ሲካሔድ በመቆየቱ፣ ውሳኔ አሰጣጡም ከላይ ወደታች የመውረድ ዝንባሌ አሳይቷል። በተለይም የተፈጥሮ ሀብትን በማስተዳደር ረገድ ከነባሩ ሕዝብ ጋር ያለው አለመተማመንና ውጥረት የጋራ ማኅበራዊ አስተዳደር እንዳይኖር እንቅፋት ሆኗል።

የሰፈራው አካባቢ መሠረተ ልማት ሠፋሪዎች ከመጡበት አካባቢ የመሠረተ ልማት ደረጃ ያላነሰ መሆን ይኖርበታል። ሆኖም ግን መንገዶችና የመገናኛ አውታሮች ከመጡበት ሥፍራ ጋር ሲነጻጸሩ በዕድገት ቀረት ያሉ ናቸው። በተያያዥም በአንዳንድ ቦታዎች በሰፋሪዎቹ መምጣት ሳቢያ ለነባሩ ሕዝብ ይሰጥ የነበረው የጤናና የትምህርት አገልግሎት ሲጓደል ተስተውሏል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ነባር አካባቢዎች ለሰፋሪዎች ታስበው በተሠሩ ጤና ጣቢያዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ወፍጮ ቤቶች እንዳይገለገሉ ተደርገዋል። በአንዳንድ አካባቢም ነባሩ ሕዝብ ወደ ተፈጥሮ ሀብት፣ ማለትም ደኖች፣ ወንዞችና የውሃ መቅጃ ቦታዎችና የከብት መዋያ ቦታዎች አካባቢ እንዳይደርስ እገዳ ተደርጎበታል።

## የጥናቱ መፍትሔ ሃሳቦች

### 1. ነባር የሰፈራ ጣቢያዎችን በተመለከተ

- ለክረምት ወራት የሚያገለግሉ መንገዶች እንዲሻሻሉ ማድረግ፣
- የምግብ ዋስትና ገና ባልተረጋገጠባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እርዳታ ማቅረብ፣
- አንድ ሄክታር ብቻ ለተሰጣቸው ሠፋሪዎች መሬት እንዲጨመርላቸው ማድረግ፣ ዕደላውም የመሬት ለምነትና የቤተሰብ ብዛትን ባገናዘበ መልኩ እንዲሆን፣
- ለተጨማሪ በሬ ግዢ የሚያስችል ገንዘብ በብድር መስጠት፣
- ከእርሻ ሥራ በተጓዳኝ የገቢ ምንጭ ሊያስገኙ የሚችሉ ሥራዎች እንዲሰሩ ሰፋሪዎችን ማበረታታት፣
- የከብት ሕክምና አገልግሎትን ማጠናከር፣
- የወባ በሽታ ስጋት እንዲቀንስ የአጎበር አቅርቦት እንዲሻሻል ማድረግ፣
- የጤና መገልገያ መሣሪያዎችና መድሀኒቶች አቅርቦታቸው እንዲሻሻል ማድረግ፣
- ለቤተሰብ ዕቅድና ለፀረ-ኤች አይ ቪ / ኤድስ እንቅስቃሴ የበለጠ አጽንኦት መስጠት፣
- የትምህርት ቤት ሕንጻዎች፣ ባለሙያዎች፣ እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሻሻሉ ማድረግ፣ ግልጋሎቱንም ለነባሩ እና ለሰፋሪ ልጆች እኩል ክፍት ማድረግ፣
- በነባሩ ሕዝብና በሰፋሪዎች መሃል የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መስተጋብር/ትስስር እንዲኖር ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት፣
- መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የጋራ የውዝግብ መፍቻ ዘዴዎችና ሂደቶች እንዲዳብሩ ማድረግ፣

- ነባሩ ሕዝብና ሰፋሪዎች የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ እንዲያስተዳድሩና እንዲጠብቁ ማበረታታት፤
- ሰፈራን በተመለከተ በመንግሥትና በአጋሮቹ መሃል የእርስ በርስ መተማመንና መተባበር እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በ1998 ዓ.ም አዳዲስ የሰፈራ ጣቢያዎችን በመመስረት ፈንታ ነባሮቹን በማጠናከር ላይ አትኩሮት ማድረግ።

## 2. ቀጣይ የሰፈራ ፕሮግራምን በተመለከተ

- የነባሩ ሕዝብ መሬት መነጠቅ ሳይኖርበት በቂ ለም መሬት መኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ፤
- የሰፈራ ጣቢያዎች በደን ወይም በዱር አራዊት ክልል አቅራቢያ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- በሰፈራው ጣቢያ አካባቢ የሚገኙ ነባር የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰፋሪውን ለመቀበል ሙሉ በሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- የነባሩ ሕዝብ የእርሻ፣ የግጦሽና የደን መሬት መብት እንዲጠበቅለት ዋስትና መስጠት፤
- የሀብት ምንጭ የሆኑት ንብረቶች መወሰድ ካለባቸው ካሣ መክፈል ወይም የተሻለ አማራጭ ማቅረብ፤
- ሊተገበር የማይችል ተስፋ ለዕጩ ሰፋሪዎች አለመስጠት፤
- “የእርዳታ እህል ይቋረጣል” ብሎ ዕጩ ሰፋሪዎችን አለማስፈራራት፤
- ሌላ አማራጭ በማሳጣት መሬት የሌላቸው ተስፋ የቆረጡ ድሆችን ወደ ሰፈራ እንዲሄዱ አለመገፋፋት፤
- የዕጩ ሰፋሪ ተወካዮች ሰፈራ ጣቢያቸውን በበቂ ሁኔታ እንዲቃኙት ማስቻል፤
- የሰፋሪዎቹ የቀድሞ መሬት ይዞታ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ መጠበቁን ማረጋገጥ፤
- ሰፋሪዎቹ ከጣቢያው ከመድረሳቸው በፊት የምግብ፣ የመጠጥ ውሃ፣ የጤና፣ የከብት ሕክምና፣ የትምህርት አገልግሎት፣ የእርሻ በሬ፣ የወባ አጎበሮች፣ ወዘተ በበቂ ሁኔታ መኖራቸውን ማረጋገጥ፤
- በተቻለ መጠን ከአንድ አካባቢ የሚመጡ ሰፋሪዎች ሳይነጣጠሉ እንዲሠፍሩ ማድረግ፤
- የምግብ እርዳታ ለሁለት ዓመት ጊዜ እንዲቀጥል ማስቻልና ወቅታዊ ግምገማ ማድረግ።

## 3. የፖሊሲ አቅጣጫን በተመለከተ

- የሰፈራ ፖሊሲን ሰፋ ካለው የዜጎች ከቦታ ቦታ ዝውውር ማዕቀፍ ውስጥ አድርጎ ማየት፤
- ልማትን ለማምጣት በሰፋሪዎቹና በነባሩ ህዝብ መሃል ትስስር እንዲኖር ማስቻል፤
- የሰፈራ መርሐ ግብረሩን መሬት የጠበባቸውን እና የምግብ ዋስትና የሌላቸውን ደገኞች የሚያገግሙበት መሳሪያ ከማድረግ ይልቅ ለቆላማው አካባቢ የወደፊት የልማት መድረክ አድርጎ ማየት፤
- የቆለኞቹ የሀብት ምንጭ መብቶች በግልጽ እንዲከበሩ የህግ ማዕቀፎችና የማስፈጸሚያ ስልቶችን ማቅረብ፤ እንዲሁም ለወደፊቱ ከሚሠፍሩት ሰፋሪዎች ጋር የጋራ ልማት እንዲኖር ማድረግ፤
- በሰፋሪዎችና በባለሀብቶች መሃል ያለው ትስስር ልማትን በሚያጎለብት መልኩ እንዲቃኝና በባለሃብቶች የሚቀጠሩ ሰፋሪዎች ዝቅተኛ ደሞዝ ወለል እንዲጠበቅ ማስቻል፤
- ወቅቱን እየጠበቀ የሚገመገም የሰፋሪዎች እርዳታ፣ ማበረታቻና ብድር አቅርቦት ሥርዓትን መፍጠር።

## 4. ለጋሾችና ዓለም አቀፍ ተቋማት

- አዳዲስ የሰፈራ ጣቢያዎች እንዲመሰረቱ ከመጣር ይልቅ ነባሮቹ እንዲጠናከሩ ጥብቅና መቆምና መደገፍ፤
- ውጤታማ ሊሆን የሚችል ወቅታዊ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መንደፍና መተግበር፤
- የቤተሰብ ዕቅድን፣ ኤች አይ ቪ /ኤድስን፣ የአካባቢ ጥበቃና ልማትን፣ የጤና አጠባበቅን፣ የከብት ሕክምናን በሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በይበልጥ መሳተፍ፤
- በሰፋሪውና በነባሩ ሕዝብ መሃል የግጭት አፈታት ሥርአት እንዲጎለብትና የጋራ ልማት ትስስር እንዲኖር ለማስቻል ከክልል መንግሥታት ጋር ተባብሮ መሥራት፤
- የከተማና የገጠር እንዲሁም የቆላውና የደጋው ትስስር የተመጣጠነ የልማት ምንጭ የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሰፋ ያለ የሕዝብ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር ማዕቀፍ እንዲዘረጋ ማድረግ።

**ምንጭ:-** Rethinking Resettlement: The Ethiopian Experience (*ወደፊት የሚታተም*)

**Address: Forum for Social Studies ♦ P. O. Box 25864 code 1000 ♦ Addis Ababa, Ethiopia**
**Telephone: 251-111-572 -990/91 ♦ Fax: 251-111-572-979**
**E-mail: fss@ethionet.et ♦ Home page: www.fssethiopia.org.et**